# ኢትዮጵያ እና ኬንያ የተፈራረሙትን የተቀላጠፈ የጠረፍ ንግድ ማዕቀፍ ለማስፈጸም በተዘጋጀው ረቂቅ መመሪያ ላይ የቀረበ አጭር መግለጫ

1. **መግቢያ**

ኢትዮጵያ እና ኬንያ በሚዋሰኑባቸው የጋራ ድንበር አካባቢ የሚኖሩ ማህበረሰቦችን በጠረፍ ንግድ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል የተቀላጠፈ የጠረፍ ንግድ ማዕቀፍ (Simplified Border Trade Regime) በሁለቱ ሀገራት መካከል ታህሳስ 10 ቀን 2018 ዓ.ም በአዲስ አበባ ላይ ተፈርሟል፡፡ የዚህ የጠረፍ ንግድ ማዕቀፍ ዋና ዓላማ በሁለቱ ሀገራት የጋራ ድንበር አካባቢ የሚኖሩ ህዝቦች ከመሀል ሀገር በቀላሉ ማግኘት የማይችሏቸውን መሰረታዊ የፍጆታ ምርቶች በህጋዊ የጠረፍ ንግድ አሰራር እንዲያገኙ ማስቻል ነው፡፡

በማዕቀፉ አንቀጽ 10 እንደተመለከተው ሁለቱ ተፈራራሚ ሀገራት የጠረፍ ንግድ ማስፈጸሚያ መመሪያ በማውጣት የጠረፍ ንግድ መተግበር እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሰረት በሀገራችን በኩል ከኬንያ ጋር የሚዋሰኑ የማህበረሰብ ክፍሎች መሰረታዊ የፍጆታ ምርቶችን በጠረፍ ንግድ መገበያየትና መጠቀም የሚያስችል የጠረፍ ንግድ ማስፈጸሚያ መመሪያ ማውጣት አስፈልጓል፡፡

የሚኒስቴር መ/ቤታችን በዚህ ዓመት በእቅድ ከያዛቸው ተግባራት መካከል ከኬንያ ጋር በተፈረመው የተቀላጠፈ የጠረፍ ንግድ ማዕቀፍ መሰረት የጠረፍ ንግድ ለማካሄድ የሚያስችል የጠረፍ ንግድ መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ ማድረግና የድንበር አካባቢ ማህበረሰቦችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የሚለው ይገኝበታል፡፡ ስለሆነም የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 35 (2) እና 52(2) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን በኢትዮጵያ እና በኬንያ የድንበር አካባቢዎች ተፈጻሚ የሚሆን ረቂቅ የጠረፍ ንግድ መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡

2. **የመመሪያው አስፈላጊነት**

የጠረፍ ንግድ መመሪያውን ማውጣት ያስፈለገበት ዋና ምክንያት ከኬንያ ጋር የተፈረመውን የተቀላጠፈ የጠረፍ ንግድ ማዕቀፍ በሀገራችን የንግድ አሰራር ስርዓት መሰረት ወደ ትግበራ በማስገባት በሀገራችን በኩል ከኬንያ ጋር የሚዋሰኑ የድንበር አካባቢ ማህበረሰቦች ከመሀል የሀገራችን ክፍሎች በቀላሉ ማግኘት የማይችሏቸውን የፍጆታ ምርቶች በጠረፍ ንግድ እንዲቀርቡላቸው ለማድረግ ነው፡፡

በተጨማሪም በድንበር አካባቢ ህጋዊ የጠረፍ ንግድ አሰራርን መተግበር በአካባቢው የሚስተዋለውን የኮንትሮባንድ እና ህገ-ወጥ የንግድ እንቅስቃሴ ለመቀነስ፣ አነስተኛ የመነገድ አቅም ላላቸው ድንበር አካባቢ ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር፣ በኢትዮጵያ እና በኬንያ ጎረቤት ሕዝቦች መካከል ያለውን ግንኙነት በማጠናከር በድንበር አካባቢ ሰላምና ፀጥታ ለማስፈን እና ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር የጠረፍ ንግድ መረጃ አያያዝንና ቁጥጥርን ለማጠናከር የላቀ ፋይዳ እንደሚኖረው ታምኖበታል፡፡

3. <u>የመመሪያው ድንጋጌዎች ይዘት</u>

ረቂቅ መመሪያው በአጠቃላይ በሦስት ክፍሎች እና በ12 አንቀጾች የተደራጀ ሲሆን በጠረፍ ንግድ የሚነገዱ የጋራ ምርቶችን የሚዘረዝር አንድ አባሪ አለው፡፡ በክፍል አንድ_ከአንቀጽ 1 እስከ 3 ባሉት ድንጋጌዎች የረቂቅ መመሪያዉን አጭር ርዕስ፣ የቁልፍ ቃላትን ትርጓሜ እና የተፈጻሚነት ወሰንን የሚመለከቱ አንቀጾችን አካቶ ይዟል፡፡

መመሪያው “የኢትዮጵያ እና የኬንያ የጠረፍ ንግድ መመሪያ” ተብሎ ሊጠቀስ እንደሚችል በአንቀጽ 1 ላይ የተመለከተ ሲሆን በአንቀጽ 2 የጾታ አገላለጽን ጨምሮ በመመሪያው በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ የዋሉ የድንበር አካባቢ፣ የጠረፍ ነጋዴ፣ የጠረፍ ንግድ ምርቶች፣ የድንበር በር እና ሚኒስቴር የሚሉት ቁልፍ ቃላት ትርጓሜ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በአንቀጽ 3 ላይ ደግሞ መመሪያው በኢትዮጵያ እና በኬንያ የድንበር አካባቢ በሚካሄድ የጠረፍ ንግድ ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን ተመልክቷል፡፡

ክፍል ሁለት ከአንቀጽ 4 እስከ 10 ያሉትን ድንጋጌዎች ያካትታል፡፡ በአንቀጽ 4 በጠረፍ ንግድ ስራ ላይ መሰማራት የሚችሉ ሰዎች የሚለዩበት መስፈርት የተቀመጠ ሲሆን በጠረፍ ንግድ የሚነገዱ ምርቶችን ዓይነት፣ መጠን እና ወርሀዊ ምልልስ የሚመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮች ደግሞ በአንቀጽ 5 ላይ ተመልክተዋል፡፡

የወጪና የገቢ ምርቶች ዋጋ ስለሚተመንበት ሁኔታ፣ በድንበር በሮች ስለሚሰጡ አገልግሎቶች እና በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር እና በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን መካከል የጠረፍ ንግድን በተመለከተ የመረጃ ልውውጥ ስለሚደረግበት ሁኔታ ከአንቀጽ 6 እስከ 8 ባሉት ድንጋጌዎች እንዲካተት ተደርጓል፡፡

- የጠረፍ ንግድ ፈቃድ አጠቃቀምን በተመለከተ የጠረፍ ንግድ ሥራ ፈቃድን በውሰት ወይም በሌላ መንገድ ለሌላ ሰው ማስተላለፍ ወይም የሌላ ሰው ፈቃድን መጠቀም ለማንኛውም የጠረፍ ነጋዴ የተከለከለ መሆኑ በአንቀጽ 9 ላይ ተደንግጓል፡፡

➢ ክፍል ሦስት ከአንቀጽ 10 እስከ 12 ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን ይዟል፡፡ በመመሪያው ያልተሸፈኑ የጠረፍ ንግድ ምዝገባ እና የንግድ ሥራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ፣ እድሳት፣ ምትክ፣ እገዳ እና ስረዛ ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈጻሚ የሚሆኑ የንግድ ሕጎች በአንቀጽ 10 ላይ የተዘረዘሩ ሲሆን በጠረፍ ንግዱ የሚነገዱ ምርቶችን ዝርዝር የያዘው ሰንጠረዥ የመመሪያው አካል መሆኑ በአንቀጽ 11 ላይ ተመልክቷል፡፡ በመጨረሻም መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ በአንቀጽ 12 ላይ ተደንግጓል፡፡

4. <u>**በረቂቅ መመሪያው ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ውይይቶች**</u>

በረቂቅ መመሪያው ላይ የሚመለከታቸው የፌዴራል እና የክልል ተቋማት ያላቸውን አስተያየት የሰጡበት መድረክ ከህዳር 1-2 ቀን 2018 ዓ.ም በአዳማ ከተማ የተዘጋጀ ሲሆን በመድረኩ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከፍትህ ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን፣ ከፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ ከኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፣ ከኢሚግሬሽንና የዜግነት አገልግሎት፤ ከኦሮሚያ ክልል ንግድ ቢሮ፣ ከሶማሌ ክልል ንግድና ትራንስፖርት ቢሮ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ንግድ ቢሮ፣ በሶማሌ ክልል ከሞያሌ ወረዳ ንግድ ጽ/ቤት፣ በኦሮሚያ ክልል ከሞያሌ ወረዳ ንግድ ጽ/ቤት፣ ከሞያሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፣ ከሞያሌ ኢምግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት ቅ/ጽ/ቤት፣ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ከዳሰነች ወረዳ ንግድ ጽ/ቤት እንዲሁም ከሚኒስቴር መ/ቤታችን የተለያዩ የስራ ክፍሎች የተውጣጡ ተወካዮች ተሳትፈዋል፡፡

በውይይት መድረኩ ከባለድርሻ አካላት ለተነሱ ጥያቄዎች ማብራሪያ የተሰጠ ሲሆን አግባብነት ያላቸው አስተያየቶች በግብዓትነት ተወስደው ረቂቅ መመሪያው እንዲዳብር ተደርጎ ተዘጋጅቷል፡፡

በመጨረሻም የሚኒስቴር መ/ቤታችሁ በረቂቁ ላይ በፌደራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሰረት የህግ አስተያየት እንዲሰጥበት የካቲት 10 ቀን 2018 ዓ.ም በቁጥር 01.1.28.1/8423 በተጻፈ ደብዳቤ በጠየቅነው መሠረት መጋቢት 14 ቀን 2018 ዓ.ም በቁጥር ፍ.ሚ-5/6728/18 በተጻፈ ደብዳቤ ምላሽ የሰጣችሁ ሲሆን ከተሰጡት አስተያየቶች ውስጥ በግብአትነት የሚወሰዱትን በመቀበል ረቂቁ እንዲዳብር ተደርጎ ለቀሪዎቹ አስተያየቶች ደግሞ በተጨማሪነት በተያያዘው ግብረ-መልስ ላይ ተገቢውን ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተናል፡፡

ስለሆነም በሚኒስቴር መ/ቤታችሁ የተሰጡ የሕግ አስተያየቶችን እና በእኛ በኩል የተሰጡ ምላሽና ማብራሪያዎችን ታሳቢ በማድረግ መመሪያው የጸደቀ በመሆኑ በፌዴራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሠረት እንዲመዘገብልን በአክብሮት አቅርበናል፡፡